# ደንብ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

ተዛማጅ ሠነዶች፦ BLB, IGS, IGT-RA, ILA-RA, IQB-RA, JFA, JFA-RA, JGA, JGA-RB, JGB-RA, JHF, JHF-RA, KBA-RA

ኃላፊነት የሚመለከተው ቢሮ፦ Division of Technology Services, Division of School Leadership and Improvement, Division of Teaching and Learning

## የግል ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) መሣሪያዎች

I. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች የግል ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) መሳሪያዎችን የመያዝ እና የአጠቃቀም ሥርዓት መደንገግ

II. ትርጉም

A. A. ለዚህ ደንብ ዓላማ የግል ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) መሳሪያ (PMD) ሶስት መለያ ባህሪያት አሉት፦

1. የመሳሪያው ባለቤትነት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ያልሆነ ወይም ከ (MCPS) ያልተሰጠ መሆን አለበት።

2. መሣሪያው መረጃ ለመላክ እና ለመቀበል የበይነመረብ፣ ዋይ-ፋይ/wi-fi፣ ወይም የተንቀሳቃሽ ስልክ/cellular ግንኙነት ማድረግ የሚቻልበት ነው።

3. መሣሪያው ድምጽን፣ ምስሎችን/ቪዲዮ ለመቅረጽ የሚያስችል ነው። የግል ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) መሣሪያዎች (PMDs) ምሳሌ ሶስቱን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሞባይል ስልኮችን፣ ኢ-አንባቢዎችን (e-readers)፣ ስማርት ሰዓቶችን፣ ታብሌቶችን፣ ተለባሽ ቴክኖሎጂዎችን፣ የቪዲዮ እና የድምጽ መቅረጫዎችን እና የመጫወቻ መሳሪያዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ፤ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ አይገደብም።

B. ርእሰመምህር/ተወካይ ማለት፦ እንደአግባቡ የአንድ ት/ቤት ወይም ጽ/ቤት ሃላፊ የሆነ(ች) አስተዳዳሪን ይመለከታል።

C. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ማለት፦ ማንኛውም ትምህርት ቤት ወይም ሌላ የ MCPS ተቋም፣ በ MCPS ባለቤትነት የተያዘ ወይም የሚመራ ቅጥርግቢን ጨምሮ፣ በ MCPS ባለቤትነት የተያዙ፣ የሚተዳደሩ፣ ወይም በኮንትራት የተያዙ አውቶቡሶች እና ሌሎች ተሽከርካሪዎች፤ ህንጻዎች/ፋሲሊቲ እና/ወይም በ MCPS መርኃግብር የተዘጋጁ ተማሪዎች የሚሳተፉባቸው እንቅስቃሴዎችን በሙሉ ይመለከታል።

D. የተማሪዎች ቀን የሚጀመረው ተማሪዎች ወደ ት/ቤት ከመጡበት ሰአት ጀምሮ እስከሚሰናበቱበት ሠዓት ነው። በተጨማሪ የተማሪዎች ቀን፦ ከስርአተ ትምህርቱ ጋር የተጣመሩ እና በ MCPS የሚደገፉ ከስርአተ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን እና በተራዘሙ ቀናት እና የተራዘሙ የትምህርት ፕሮግራሞችን ለሚከታተሉ ተማሪዎች የማስተማሪያ ጊዜን ያካትታል።

## III. ዳራ

ህጻናትን በበይነመረብ ከሚደርስባቸው ጥቃት የመከላከል የፌደራል ህግ (CIPA) ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ጎጂ የበይነመረብ ይዘትን አጠቃቀም ለመገደብ ትምህርት ቤቶች የመከላከያ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይደነግጋል። በትምህርት ቤት የግል ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) መሳሪያዎች – መረጃ ለመላክ እና ለመቀበል ኢንተርኔት፣ ዋይ-ፋይ/wi-fi ወይም ሴሉላር ግኑኝነትን የማድረግ አቅም ያላቸው – የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመቆጣጠሪያ እርምጃዎችን በመጣስ ታዳጊ ልጆችን የሚጎዳ ይዘት ያላቸው መረጃዎችን በቴክኖሎጅያዊ መሣሪያ የማግኘት እና የማስተላለፍ ወይም የማሠራጨት ሂደትን ለመገደብ የሚደረገውን ጥረት በመጣስ አገልግሎት ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች ናቸው።

በተጨማሪም፣ በትምህርት ቀን በህጋዊነት ለትምህርታዊ ዓላማ ከመጠቀም ያለፈ ኢንተርኔት እና ማህበራዊ ሚዲያን መጠቀም የትምህርት ሥራን እና የተማሪን ትምህርት ሊያስተጓጉል ይችላል። ተማሪዎች የግል ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) መሳሪያዎችን መጠቀም የሚችሉበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ እና የአጠቃቀም ዘይቤ ሥርዓት መመስረት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የመማር እና የማስተማር ሂደት በአግባቡ እንዲተገበር ለመጠበቅ ስለሚረዳ፥ በተማሪ የግል ሞባይል/ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች አጠቃቀም ላይ ምክንያታዊ እና ከእድሜ ጋር የሚመጥኑ ገደቦችን ማስቀመጥ አንዱ ጠቃሚ እርምጃ ነው።

## IV. የሲስተም ቁጥጥር/አስተዳደር

A. MCPS የፌደራል ህግን በማክበር ረገድ፣ የተማሪዎችን ጎጂ የበይነመረብ ይዘት ተደራሽነት ለመገደብ ማጣሪያ እና ሌሎች የቴክኖሎጂ እርምጃዎችን ይጠቀማል።

B. ሁሉም የ MCPS መሳሪያዎች፣ የ MCPS አውታረመረብ እና የተማሪዎች የ MCPS አውታረ መረብ አካውንቶች የ MCPS ንብረቶች በመሆናቸው ለትምህርታዊ ጉዳዮች ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፤ እና ክትትል ሊደረግባቸው፣ ሊመዘገቡ፣ እና በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው።

C. MCPS በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አውታረ መረብ ላይ ሁሉንም PMDs እና PMD አጠቃቀም ይከታተላል/ይቆጣጠራል፤ እና አጠቃቀማቸውን የመመርመር መብቱ የተጠበቀ ነው።

D. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውታረመረብ ወይም ስራዎች ላይ መስተጓጎልን በሚፈጥር መልኩ PMD መጠቀም ለሰራተኞች እና ለተማሪዎች የተከለከለ ነው። ተማሪዎች እና ሰራተኞች PMD ሪኮርዶችን በመቀየር፣ የኤሌክትሮኒክስ ንብረት ማበላሸት/ማጥፋት ወይም ሌሎች ተዛማጅ ጥፋቶችን መፈፀም የዲሲፐሊን ቅጣት ሊያስከትልባቸው ይችላል።

## V. ሃላፊነት/ተጠያቂነት

MCPS ለማንኛውም የተንቀሳቃሽ/ሞባይል መሳሪያ መጥፋት፣ መሠረቅ፣ ወይም ብልሽት ወይም ያልተፈቀደ PMD አጠቃቀም ምንም አይነት ሃላፊነት ወይም ተጠያቂነት አይኖርበትም።

## VI. ሂደቶች – MCPS ንብረት ላይ የተማሪ የግል ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) መሳሪያዎች

A. የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎችን መያዝ

1. ተማሪዎች በ MCPS ቦታዎች እና MCPS በሚያዘጋጃቸው መርሃግብሮች ላይ PMDs መጠቀም ይችላሉ።

2. MCPS ንብረት ላይ መረጃ ለመላክ ወይም ለመቀበል PMD የሚጠቀሙ ተማሪዎች ሕግ፣ የቦርድ ፖሊሲዎችን፣MCPS ደንቦችን እና (ከዚህ በኋላ "MCPS ደንቦች" ተብለው የሚታወቁትን) መስፈርቶች ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

3. MCPS ደንብ JGB-RA ፍተሻ እና መያዝ ድንጋጌ መሠረት፥ MCPS ህጎች ጋር በማይጣጣም መልኩ PMDs ጥቅም ላይ ከዋሉ በትምህርት ቤት ባለስልጣናት ፍተሻ ተደርጎ ሊወሰዱ ይችላሉ።

B. የተፈቀደ የግል ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) መሳሪያዎች አጠቃቀም

MCPS ንብረት ላይ PMDs ስለመጠቀም ተማሪዎች የሚከተሉትን ህጎች የማክበር ግዴታ አለባቸው። ተማሪዎች መጠቀም ባልተፈቀደላቸው ወቅት PMDs ዘግተው በማይደርሱበት ቦታ የማስቀመጥ ሃላፊነት አለባቸው።

1. ርዕሰ መምህራን/ወኪሎች ስለ PMDs አጠቃቀም የመፍቀድ ውሳኔ የሚሰጡት በሚከተለው ሁኔታ ነው።

   a) MCPS ህጎች ጋር በማይጣጣም መልኩ ጥቅም ላይ ከዋሉ ርእሰ መምህራን PMDs በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ እያሉ እንዳይጠቀሙ ለጊዜው ማገድ ይችላሉ።

   b) ርእሰ መምህራን ከትምህርት ቤት አመራር ቡድን ጋር በመተባበርለማስተማር እንዲጠቀሙ መፍቀድ ይችላሉ።

   c) የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) የተማሪ እና የሰራተኞች PMDs በመደበኛ የፈተና አካባቢዎች መጠቀምን ይከለክላል፣ እነዚህም የፈተና አሰጣጥ ደህንነት ላይ አደጋ ይኖራቸዋል ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

      i) MCPS ደንብ ILA-RA፣ ከደህንነት እና ሪፖርት ማቅረብ መስፈርቶች ላይ የተደረጉ ግምገማዎች፣ ተማሪዎች ደረጃቸውን በጠበቁ ፈተናዎች ወቅት PMDs እንዲጠቀሙ የመፍቀድ የተወሰኑ ነፃነቶችን ይገልጻል።

      ii) ከደህንነት እና ከሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶች ጋር በሚደረጉ ምዘናዎች ወቅት ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ PMDs አጠቃቀም ላይ ከጋራ ተጠያቂነት ክፍል ይሁንታ ማግኘት አለባቸው።

   d) ርእሰ መምህሩ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በመመካከር ግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም ወይም 504 ፕላን ለሌለው/ለሌላት ተማሪ እንደዚህ አይነት አጠቃቀሞች ILA-RA ውስጥ ካልተገደበ በስተቀር PMD አኮሞዴሽን እንዲሰጥ መፍቀድ ይችላል።

   e) ርእሰ መምህራን ተመሳሳይ የሆኑ መሳሪያዎችን ነገርግን ከላይ እንደተገለጸው የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያ አጠቃቀም ሁሉንም መመዘኛዎች ባያሟሉም ለመጠቀም ፍቃድ ከመስጠታቸው በፊት ከትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ ክፍል (DSLI) እና ከቴክኖሎጂ አገልግሎት ዲቪዥን (DTS) ጋር ማማከር አለባቸው። DSLI እና DTS ከላይ በተገለጸው መሰረት ሁሉንም PMDs ተግባራዊ መመዘኛዎች የማያሟሉ ለልጆች አጠቃቀም ተገቢነት ያላቸው የመገናኛ መሳሪያዎችን ለንግድ ፈጠራ መመሪያ ለማዘጋጀት መተባበር አለባቸው።

f) ደንብ KBA-RA ህዝባዊ መረጃ ላይ እንደተገለጸው ርእሰ መምህራን ተአማኒነት ያለው፣ ይፋዊ መረጃን ወቅታዊ እና በተሟላ መልኩ ስለማሳወቅ ከግንኙነት ክፍል "Division of Communication" ጋር መተባበር አለባቸው።

2. በአውቶቡስ ጉዞ ላይ መጠቀም

ተማሪዎች በ MCPS አውቶቡሶች ወይም በ MCPS ባለቤትነት የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ላይ ወደ ትምህርት ቤት ሲጓዙ ወይም ከትምህርት ቤት በሚመለሱበት ወቅት አጠቃቀሙ የአውቶቡሱን ጉዞ ደህንነት ካላደናቀፈ እና MCPS ህጎችን እስካልጣሱ ድረስ PMDs መጠቀም ይችላሉ።

3. አንደኛ ደረጃ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

a. የአንደኛ ደረጃ እና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች PMDs ከተማሪ የትምህርት ሠዓት በፊት እና በኋላ ሊጠቀሙ ይችላሉ።

b. የአንደኛ ደረጃ እና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በትምህርት ሰዓት፣በምሳ ሠዓት፣ ወይም በክፍሎች የፈረቃ ወቅት መጠቀም አይፈቀድላቸውም።

4. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ከተማሪ የትምህርት ሠዓት በፊት እና በኋላ፣ በክፍል ፈረቃ የሽግግር ጊዜ እና በተማሪ የምሳ ጊዜ ውስጥ PMDs መጠቀም ይችላሉ።

## VII. በሃላፊነት የመጠቀም መርሕ

A. የሌሎች ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን እንቅስቃሴ በሚያውክ ሁኔታ ወይም የ MCPS ህግ በሚጥስ መልኩ ተማሪዎች ቴክኖሎጂን ከመጠቀም መቆጠብ አለባቸው።

B. PMD በመጠቀም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ህጎችን የጣሰ(ች) ማንኛውም ተማሪ MCPS የተማሪ ስነምግባር ህግ መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል።

C. የቦርድ ፖሊሲ JHF፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት፣ከ MCPS ንብረት ውጭ የሚፈፀም የስነምግባር ጥሰትን ጨምሮ፣ ከትምህርት ቤት መቼት ጋር ግንኙነት ያለው፣ የትምህርት አካባቢው በአካል ወይም ቨርቹዋል ቢሆንም፤ ምግባሩ ሌሎች ተማሪዎች በትምህርት ላይ እያሉ የመጉዳት አደጋን ስለሚፈጥር ወይም ምግባሩ የትምህርት አውድ ላይ ጣልቃ በመግባት የሚያስተጓጉል ስለሆነ የሳይበር ጉልበተኝነትን ይከለክላል።

D. MCPS ደንብ IGT-RA፣ ለኮምፒዩተር ሲስተም፣ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ እና የአውታረ መረብ ደህንነት የተጠቃሚ ሃላፊነት፣ MCPS ንብረት ላይ PMDs ለሚጠቀሙ ተማሪዎች የተደነገገው ኃላፊነት የተሞላበት የአጠቃቀም መመሪያ እንደሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል።

1. ተማሪዎች በማንኛውም ጊዜ PMDs ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማስቀመጣቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

2. መረጃው የሌሎችን ግላዊ ገመና የሚጥስ፣ የተማሪዎችን ወይም የሰራተኞችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል፣ ጸያፍ ወይም ስድብ ከሆነ፣ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ወይም የ MCPS ስራዎችን የሚያስተጓጉል ከሆነ፣ የአካዳሚክ ታማኝነት የጎደለው ከሆነ ወይም MCPS የኮምፒዩተር ሲስተምን፣ ተዛማጅ ቴክኖሎጂ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን ደህንነት የሚጥስ ከሆነ PMD በመጠቀም ግንኙነት/ኮሙኒኬሽን ማድረግ አይቻልም።

    a) ይኼውም የራስን እና የሌሎችን ግላዊ ገመና የተማሪን ግላዊ መረጃ እና የሌሎችን ግላዊ መረጃ (የትምህርት ውጤቶችን፣ የቤት/የሞባይል ስልክ ቁጥር፣ የፖስታ አድራሻ እና የተጠቃሚ የይለፍ ቃሎችን ጨምሮ) ማቆየትን ያካትታል፥ ነገር ግን በዚህ ብቻ አይገደብም።

    b) የአካዳሚክ ታማኝነት የጎደለው ድርጊት ላይ ያለው ክልከላ፣ ስም ማጥፋትን፣ የተማሪ ሪከርዶችን መቀየር፣ ወይም ምዘናዎችን ማሰራጨትን ያካትታል ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም።

3. ተማሪዎች MCPS አውታረመረብን/ኔትወርክን በምርታማነት፣ በአግባቡ፣ እና ከትምህርት ቤት ሥራ ጋር ለተያያዙ ዓላማዎች ይጠቀማሉ።

4. ተማሪዎች የሌሎችን የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎች መቀየር ወይም መሰረዝ የለባቸውም።

5. ተማሪዎች ከአግባብ ውጭ የሆነ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ወድያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Family Educational Rights and Privacy Act, 20 U.S.C §1232g; Protection of Pupil Rights Amendment (PPRA), 20 U.S.C. §1232h, 34 CFR Part 98, (2000 and Supp. IV 2004); Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973, as amended, 29 U.S.C. Sec. 794; Americans with Disabilities Act (ADA), 42 U.S.C. 12131 et seq.; Children's Internet Protection Act (CIPA), 47 U.S.C. §254(h)(5)(B)-(C), 254(l); Children's Online Privacy Protection Act of 1998 (COPPA), 15 U.S.C.6501-6505, 16 CFR Part 312; Public Information Act of Maryland, Ann. Code of Maryland, General Provisions Article §§4-101 through 4-601; Maryland Student Data Privacy Act of 2015, Ann. Code of Maryland, Education Article, §4-131, 7-308, and 7-443; Code of Maryland Regulations §13A.03.02.03.B(8), §13A.06.05.02-.04, .06, and §13A.08.01.14; Maryland Digital Learning Standards, Maryland State Department of Education (MSDE), May 2019; Technology Education Standards: Grades 6-12, MSDE, January 2016; Health and Safety Best Practice Guidelines: Digital Devices, MSDE, July, 2019; International Society for Technology in Education Standards Administrators, Education Leaders, Educators, and Students

**የደንቡ ታሪክ፡-** አዲስ ደንብ፣ ኖቨምበር 6, 1992፣ ጁላይ 23 ቀን 1997 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 20 ቀን 1998 ከለሳ ተደርጓል፣ ሜይ 24, 2000 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበት 16 ቀን 2001 ተሻሽሏል፣ ኦገስት 15 ቀን 2002 ተሻሽሏል፣ ጁላይ 11 ቀን 2003 ተሻሽሏል፣ ዲሰምበር 22 ቀን 2005 ተሻሽሏል፣ ጁን 12 ቀን 2007 ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 23 ቀን 2012 ተሻሽሏል፣ ጁን 28, 2017 ተሻሽሏል፣ ሜይ 2, 2022 ተሻሽሏል። ጃኑዋሪ 26, 2024 ተሻሽሏል፣ ሜይ 9, 2025 የተሻሻሉት ቴክኒካዊ ዝማኔዎች ጁላይ 1, 2025 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናሉ።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኸውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ። በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
| --- | --- |
| Director of Student Compliance and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድጅንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Division of Specialized Support Services,<br>School Counseing Services Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |

| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
| --- |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity an Organizational Development, Student Compliance and Appeals<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።
**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።
***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-
U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481,1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ሀምሌ 2024